ANUAK JUSTICE COUNCIL

*Justice, Peace and Freedom*

---

# Obang Metho's Message to Ethiopian Muslim Leaders

### Badr 8th Annual Conference in Toronto, Canada

### "Challenges and Opportunities for Ethiopian Muslims as Advocates for Human Rights in Ethiopia: Ethiopia Needs You!"

July 25, 2008

**Assalamu alaikum wa rahmatu Allah wa barakatuh**--Peace be onto you!

## አሰላም አሊኩም ውራህሙቱ አላህ ወበረከቱ!
## ሰላም ለሁላችሁ ይሁን !

## ከኦባንግ ሜቶ

(ትርጉም መላኩ ፀጋዬ መኮንን)

ኢትዮጵያውያን እስላሞች "የሚቋቋሚቸውን ውጣ ውረዶችና እድሎች ወይም ገጠመኞች" በሚዳስሰው ጉባኤአችሁ ሀሳቤን እንድገልፅ እድል ስለሰጣችሁኝ የተሰማኝ ልባዊ ስሜት ጥልቅ ነው።በጉባኤው ላይ በአካል ተገኝቼ በኢትዮጵያ ሕብረተሰብ የእናንተን ጠቃሚ ድርሻ ለመግለጽ ባለመቻሌ እያዘንኩ ሆኖም ለወደፊት ይኸው እድል ይኖረኛል የሚል ተስፋ ባሰፊው አለኝ።

በቅድሚያ የኢትዮጵያ እስላሞች፤ ክርስቲያኖችና አይሁዳዊያን በሰላምና በመፈቃቀር ለምዕተ አመታት አብረው በኖሩበት ኢትዮጵያ ውስጥ የሀገራችን እስላሞች የሕብረተሰብ ታሳትፎ የሚገጥሙትን ወጣ ወረዶች መቋቋምና መልካም አጋጣሚዎችን በመፍጠር ሊኖራቸው የሚገባውን ተሳትፎ በተገቢው በመጠቀም የሚቻልበትን ጉዳይ የሚዳስሰው ይህ ጉባኤ ለኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች መልካም አጋጣሚ ነው።

አላህ ይህን ጉባኤ ይቀድሰው! ጥበብን፤ ሰላምን እውነትንና ጥንካሬን እንዲቸር ይህም ለሀገራችን፤ለአፍሪካንና መላ አለምን እንዲቀድስ እመኛለሁ። በቅዱስ ቁራን እና በመፅሃፍ ቅዱስ እንደተገለጸው (1 ፡ 5- 6) "እነርሱ ይስራሉ እኛ ለእርዳታ እንማፀናለን እኛንም በትክክለኛ ጎዳና እንድንመራ ጠብቀን" ይላል

ይህ ጉባኤ ብዙ ጉዳዮችን እንደሚሸፍን አዉቃለሁ። የእስልምና ታሪክን፤ የኢትዮጵያ እስልምና እምነትና ማንነት፤ የጤና ጉዳዮች፤የወጣቶች ጉዳይን ወቅታዊ ሁኔታዎች በመሳሰሉት እርሶች ላይ ውይይት ይደረጋል። ከዚሁም ጋር በተያያዘ መልኩ በጥሞናና በጥንቃቄ እንድትነጋገሩበት የማበረታታው እኔ ከቆምኩለት አላማ ጋር የሚሄደውን የስብአዊ መብት ጉዳይ ነው።

እኔን ለማታውቁኝ ሰሜ ኦባንግ ሜቶ ይባላል። የአኙዋክ የአለም አቀፍ የፍትህ ምክር ቤት ዳሬክተር ነኝ።ይኸውም የተወለድኩበት የአኙዋክ ሕዝብ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ጦር ሰራዊት እና በጋምቤላ ሕዝባዊ ሰራዊት ጭፍጫፋና የዘር ማጥፋት ከተፈፀመባቸው ከታህሳስ 1995 ዓ.ም ጀምሮ በዚሁ ጉዳይ ተሳትፎ እያደረኩ ነው። አኙዋክ በጣም እናሳ ብሄረሰብ ነው። ድምፃቸው አልተሰማም፤ ስቃያቸውንና መከራቸውን፤ ውጋታቸውን ሰቆያቸውን ከራሳቸው ውጭ ሌላው ባሊህ አላላቸውም።

ለአለም አቀፉ ሕብረተሰብ ይህንኑ ለማሳወቅ ስጥር በመላ ሀገሪቱ ተመሳሳይ የሆነ የፍትህ መጓደል፤ የሰብአዊ መብት ጥሰጥና ጭቆና መኖሩን ተገነዘብኩ። በዚህ ረገድ ፍትህ፤ ነፃነት፤ ሰብአዊ መብት በመላው ኢትዮጵያ እስካልሰፈነ ድረስ ለእኝዋክ ብቻ የሚመጣ ፍትህ ነፃነትና ሰብአዊ መብት መከበር አለመኖሩን ተረዳሁ። ለዚሁም ነው ዛሬ ለመላው ኢትዮጵያ ያለምንም የጎሳ፤ የባህል፤ የክልል፤ የሀይማኖት ወይም የፆታ ልዩነት ቆሜ የምሟገተው፤ የምናገረውና የማስረዳው መልክቴንም የላኩላችሁ በዚህ ምክንያት ነው።

በአሁኑ ሰዓት እናኳ በአፋር፤ በኦሮሚያ፤ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፤ክልሎችና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች በተለይም በኦዴንና በሱማሌ ውስጥ የሰብአዊ መብትን የጣሰ ግፍ እየተፈፀመ ነው። የሰብአዊ መብት ጥሰት ብቻ አይደለም እየተፈፀመ ያለው የአላህ ህግና መርህ እየተጣሰ ነው። የአላህን ሕግጋት የሚፈሩና የሚያከብሩ ሁሉ ይህን የፍትህ መጣስ ጉዳያቸው አድርገው በተግባር መቃወም ይጠበቅባቸዋል።

አኝዋኮች በተገደሉ ጊዜ ማንም ጉዳዩን አልተናገረም፤ አሁን የእኛ ድርሻ ነው በሀገራችን ለሚሳቃዩ ወገኖች መጮህ መናገር። ለምሳሌ መንገድ ላይ አንድ ሰው ቢቆስል ቁስለኛውን ከመርዳታችን በፊት ከየት ጎስ አከባቢ እንደመጣ ወይም የየት ክልል ሰው ወይም የማንኛው ሀይማኖት ተከታይ እንደሆነ የሚጠይቅ የለም። እኔ በጣም ጠንካራ የክርስቲያን እምነት ተከታይ ነኝ። እምነታችንም ከየእለት ተግባራችን ላይ ከትንሹ እስከ ውስብስቡ ችግር ሊያንፀባርቅ ይገባል። እንደእኔ እምነት በዚህ አባባል ትስማማላችሁ ባይ ነኝ። ኢትዮጵያ በከፍኛ ቀውስ ውስጥ ከመዘፈቋ የተነሳ ሊፈነዳ የሚችል ደረጃ ላይ ደርሷል። ታዲያ እንዴት ነው ሁኔታው ከቁጥጥር ስር ሳይወጣ የመፍትሄው አካል የምንሆነው?

ሕዝባችን ከሰሜን ደቡብ፤ ከምስራቅ፤ ምዕራብ ልክ እንደ ኦጋዴን በገፍ የሰብአዊ መብት ግድፈት እየተሰቃየ ነው።የሰብአዊ ቀውስ ውስጥም ገብቷል። አሁን በአጭሩ “የተዳፈነው ዳርፉር” ነው ኢትዮጵያውያን በድርቅና በምዝበራ አሰራር፤ በሰብአዊ መብት ጥሰት፤ በብልሹ አስተዳደር፤ ችግር የለም ብሎ በመካድ፤ በመንግስት ችግር እንደሌለ በማስመሰል እና በመጥፎ አገዛዝ የተነሳ ሕዝባችን በረሃ አለንጋ እየተሸነቆጠ ነው። ሀይማኖት ያላቸው ሰዎች በግልፅ ወጥተው ስለ ሰዎች መልካም ደህንነት መናገርና ከጎናቸው መቆም አለባቸው።

የኢትዮጵያ የሀይማኖት መሪዎች በጣም ወሳኝ የሆነ ስራ አለባቸው። የሰውን መብት የሚገፈውን ማስቆምና መረዳት ያለባቸውን ሰዎችን መርዳት ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ክርስትና እና እስልምና ሀይማኖቶች የታወቁ ወይንም በብዙ ኢትዮጵያዊያን የሚታመኑ ሀይማኖቶች ናቸው። ሁለቱም ሀይማኖቶች ወደ 50% የሚሆን ተከታዮች አሏቸው።

አሁን በዚህ ጽሁፍ ማስተላለፍ የምፈልገው መልክት የእስልምና መሪዎች እና ተከታዮቹ ለነፃነት፤ ስለሰዎች መብት፤ ፍትህ፤ እኩልነት እና ህግ ለሁሉም ኢትዮጵያዊያን እንዲሆን በሞራል እንዲነሱ እና እንዲቀሳቀሱ የምናምንበትን ለድርድር ካቀረብነው ወደፊት ሳናደርግ በመቅረታችን እንፈረድበታለን ።

የኢትዮጵያ የሀይማኖት መሪዎች ይህንን ሰበዊ ቀውስ ለመቋቋም እርዳታ የሚሹትን በማገዝ ብርቱ ሚና አለባቸው። የሰዎች መብት የተመሰረተው ሁሉም ሰዎች የአላህ ወይንም የእግዚአብሔር  የተወካዮች ናቸው በሚለው መሰረት ሲሆን ይህም ኦሮሞ፤ትግራይ፤አማራ፤ አፋር፤ ኦጋዴን፤ ኮንሶ ፤ ሀመር ፤ሙርሲ፤ ቦዲ፤ አሪ፤ ጀጀሮ ፤ጉጂ ሲዳማ፤ አኝዋክ፤ኒዎር፤አገው...ወዘት ወዘተ እና ሁሉም 80 የተለያዩ የኢትዮጵያ የጎሳ ማህበረሰቦች የሚኖሩባት ሀገራት ናት። ማለትም ሀብታምና ደሀ፤ ያልተማረም ሆነ የተማረ፤ እሰላሞችም ሆኑ የማያምኑትም፤ የወያኔ ሀርነት ትግራይ አባላትም ሆኑ ወያኔ ያልሆኑትም። በቁራን ወስጥ እንደሰፈረው አንድ ሰው የሰውን ደም ካፈሰሰ የሚታየው ሁሉንም ሰዎች እንደገደለ ነው ምክንያቱም የሰው ሕይወት በጣም ክቡር ስለሆነ ነው።

አላህ ሁሉንም የፈጠረውን ይወዳል። 99.9% ሰው የሚል ነገር የለም። ሁሉም ሰዎች ሙሉ ሰዎች ናቸው። ሁሉም ሰዎች ለአላህ ውድ ናቸው።ለአማኞች ይህ ምን ማለት ነው በሀገር ቤትም ሆነ በውጭ የምንኖር ኢትዮጵያዊያን ህግን ማክበርና የሌሎችን መብት በመጠበቅ እጃችንን ለአላህ ሰጥተን መኖር አለብን?

ለብዙ ምዕተ አመታት ኢትዮጵያ በአፍሪካና በመላው አለም አስገራሚና ልዩ ስፍራ ይዛ ትገኛለች። ይኸውም በእስላሞች፤ በክርስቲያኖችና በአይሁዳዊያን እምነት ተከታዮች መካከል በሰላም በጉርብትና አብረው በመኖር፤ በጋብቻ በመተሳሰር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቄስና የእስልምና ኢማም አንድ ሕንፃን በአጥር ብቻ ተከፋፍለው በበርካታ የሀገራችን ክፍል አብረው ኑረዋል።አሁንም እየኖሩ ነው።

የሆነ ሆኖ አንዳንድ ፓለቲከኞች በአሁኑ ወቅት ሀይማኖትን የራሳቸውን የፓለቲካ መርሀ ግብር ለማስፈፀም ይጠቀሙበታል። ልክ መለስ ሽብርተኝነትን እዋጋለሁ ብሎ የራሱን ሕዝብ እንደሚያሸብረው ማለት ነው። ሆነ ብለው በሕዝቡ መካከል ክፍፍል እንዲኖር፤ ጥላቻ እንዲበቅል እና የራሳቸውን ስልጣን ለማደላደል የሀይማኖት ተቋማትን ሳይቀር የዚህ አይነት አሰራር ተጠቂዎች እንዲሆኑ እያደረጉ ነው። እዚህ ላይ የአላህን ክብር የማይቀበልን ልብና ሕሊና በመስጊድና በአብያተ ክርስቲያናት ማፅዳት አለብን። በቅዱስ ቁራን (49.13) ላይ እንደተጠቀሰው"ከወንድና ከሴት እንድትፈጠሩ አደረግን፤ በመቀጠልም ጎሳዎችና ሀገራት እንድትሆኑ አስቻልን፤ ይህ እርስ በእርሳችሁ እንድትተዋወቁ በአላህ ፊት በጣም ታላቅ ክብር በጣም ትክክልና ፍጹማዊ የፍትህ ሰው ስትሆኑ ነው። አላህም ሁሉን እንድናስተውል ጥበብ ሰጥቶናል"

ለምሳሌ መለስ በኢትዮጵያ ስልጣን ላይ ሳይወጣ እስላም ክርስቲያንን ገደለ ወይም ክርስቲያን እስላምን ገደለ የሚል ታሪክ አልነበረም። ነገር ግን አሁን መለስ በኦጋዴንና በሱማሊያ አሸባሪዎችን ለመፈለግ በሚል ሰበብ ሰላማዊ ነዋሪዎችን መግደሉን ሕጋዊ ለማስመሰል እየጣረ ነው። አሁን እየፈፀመ ያለው ብዙዎቹም ባይሆኑ ጥቂቶች በኢትዮጵያ ጦር ሀይል ውስጥ የጥፋት ወኪሎች በመሆን ሰላማዊ ሞስሊሞችን እያጠቁ ነው። ይህ ጥቃት ሴቶችን፤አረጋዊያንንና ሕፃናትን ሳይቀር ያጠቃለለ ነው፡ ሴቶች በመኖሪያ ቤታቸው ይደፈራሉ። አዝመራ እንዲወድም ይደረጋል እንስሳት ይዘረፋሉ።ይህ የሞራል ተወቃሽነት ያልታከለበት አሳዛኝ ድርጊት በመሆኑ ሁላችንም ድምፃችን ከፍ አድርገን ልንቃወመው ይገባል። የታህሳስ የሱማሊያን ወረራ ተከትሎ የክርስትያኖችና የእስላሞች ፀብ ለማስመሰል በኦሮሚያ የተካሄደው የተቀነባበር ሙከራ ነበር። እኔ በግሌ ከዚህ አደጋ ሰለባዎች መካከል ያነጋገርኳቸው ምስክሮች ዘገባ መሰረት የድርጊቱ አቀንቃኖች የመለስ ድጋፊዎች መሆናቸውን አረጋግጠውልኛል እነዚህም መደበኛ ጦሩ አባላትና የደህንነት ክፍሉ በአመፁ ጀርባ እንደነበሩበት እና ይኸውም ልክ የሀይማኖት ግጭት ለማስመሰል የተካሄደ ትእይነት ነው፡ ይህም እርምጃ ሱማሊያን ለመወራር ተጨማሪ ምክንያት ለመፍጠር የታቀደም ሀሳብ ነው።

እንደክርስቲያንነትቴ ይህንን በወገኖቼ ኢትዮጵያዊያንና በሱማሌዎች የእስልምና ተከታይ ወንድሞችና እህቶች መካከል የተፈፀመን ተንኮል ለማጋለጥ እጽፋአለሁ በሚከተለው የኢንተርኔት መረብ ልታገኙት ትችላላችሁ http:// www. Anuakjustice.org/061101planToDicideMuslimsAndChrristians.html orhpp;//www.Anuakjustice.org/070525EthiopianReligiousLeadersCallOurPeopleToPrayer.html.

ስለ ለፍትህ መናገር የትኛውም ሀይማኖት ተከታይ መሆን አይጠይቅም ለምሳሌ ከአኝዋክ ጭፍጨፋ ጀምሮ ብዙ ኢትዮጵያዊያን በግል የተሰማቸውን ሀዘን በመግለፅ ለሕዝቡ ያላቸውን ድጋፍ ገልፀዋል። ይህም የኦጋዴን፤ የአፋር፤ የኦሮሞ እስልምና ተከታይ ወንድሞችና እህቶች ያካተተ ነው። እኛ ኢትዮጵያዊያን በየእምነታችን ሕዝቡን በሀይማኖት አሳበው እንዳይጠቀሙበት መከላከል ይኖርብናል በዚህ መንፈስ ዛሬ የእስልምና መሪዎች ለእምነት ለፍትህና ለመብት ከቆሙና፤ ከድሮዋ ዩጎዝላቪያ መማር ከቻልን ከእንደዚህ አይነት አደጋ ስር ልንወድቅ አንችልም

በሰላም አብሮ የመኖርን ታሪካዊ ስጦታ መሰረት አድርጋችሁ ዛሬ በእስልምና ሀይማኖት ስር ተደራጅታችሁ በኢትዮጵያ በቀና መንገድ አስተዋጮ ለማድረግ መነሳታችሁ ካስደሰተኝ ጉዳይ አንዱ ምክንያት ይህ ነው፤ ይህ ብቻ አይደለም እውነታው ይህ ድርጅት ለሁሉም ኢትዩጵያውያን የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች የየትኛውም ጎሳ፤ ባህላዊ አመጣጥ ወይም የፓለቲካ አመለካከት ሳይለይ የቆመና ከተለያዩ ማህበረሰብ ክፍሎች በመምጣታቸው ብቻ አንድ ላይ ለመስራት ለማይፈልጉ ትልቅ መልክት ያለው መሆኑ ነው። እኔ እንደሰማሁት ካሆነ ይህንን ጉባኤ የምትካፈሉት ከመላው ሀገራችን እና በውጭ የሚኖሩ የተለያዩ ሀገራት የተሰባሰባችሁ ኢትዮጵያውያን መሆናችሁ እራሱ አንድ ክንውን ነው።

እኛ ኢትዮጵያዉያን የተለያዩ መነሻ ያላቸው ማህበረሰቦና ባህርያት የያዙ ሰዎች ያሉበት አንድ ቤተሰብ ነን። በኢትዮጵያ መሬት ላይ በልዩ ልዩ ቀለማት ያሸበረቁ፤ በቁመትና በመጠን የተለያዩ አበባዎች እንድሚገኙ ማለት ነን።በሀይማኖት መለያየትበእስልምና፤በክርስቲያን ፤በይሁድ፤ በባህላዊ እምነት ወይም ሀይማኖት የማይከተሉ ሁሉ ጠላት ሊሆኑ አይገባም። ይልቁንስ ለተሻለች ኢትዮጵያና ለልጆቻችን በአንድነት እንስራ! ልክ አሁን እንደተሰባሰችሁት ሁሉ ይህን መልክትና እምነት ለሌሎች ወደ መጣችሁበት ስትመለሱ ማስተላለፍ በአስቸኳይ መጀመር አለባችሁ።

በቁራን እስላም፤ ክርስቲያንና በአይሁዳዊያን ሁሉም ከአንድ ግንድ ነው የመጣው። ይኸውም ከአላህ/ ከጦራህ አምላክ /2፡/36/ ይላል “በአላህ እናምናለን ከላይ ለእኛ የተላከ ነው። ለአብርሀም ለእስማኤል ለኢሳቅ ለያይቆብ እና ለሌሎችም ጎሳዎች ለሙሴና ለእየሱስ እንዲሁም ለመልክተኞች ከፈጣሪያቸው የተላከ ነው። እኛ ከማንናቸውም ልንለይ አንችልም ለእርሱ እኛ ተቀባይ እስላሞች ነን”

እኛ የወንድሞቻችን ጠባቂዎች ነን በቅዱስ ቁራንም እንደሚለው ደካሞችን መታደግ አለብን፤ ፈቶችና አስዳጊ ያጡ ሁሉ ፍትሀን ጥሩ መስራትን እንዲማሩ፤ ትህትና ማስየትና እራሳችን ዝቅ ማድረግ ይኖርብናል፡ እኛ እውነትን እንናገር የይቅርታ ሰዎች እንሁን፤ በፍትህ ማስተዳደር ብሎም እርስ በእራሳችን እንዋደድ፤ አንድ ተነስቶ ቢጠላ ወይም ጥላቻና ፀብ ቢሞክር ይህ ሁኔታ ለወደፊቷ ኢትዮጵያ በጣም አደገኛ መሁኑን አስተምሩት።

ልክ እንደ ናይጀሪያ አንዱ አንዱን ሲገደል ሌላው ማቆሚያ በሊለው ብቀላ ሰገዳደል እንደሚኖር መሆን የለብንም። ይህ ጥላቻ ቤተሰብንና ሕብረተሰብን እንዲበታትን አንፈልግም። በተፃራሪው የኢትዮጵያ የእምነት ሰዎች እንዴት በሰላም አብሮ መኖር እንደሚቻል ለሌሎች አፍሪካዊያንና ለሌላውም አለም በማሳየት የተቀደሰ የወንዝ ውሀ የሚፈስበት ሀገር መሆናችንን ማስመስከር ይኖርብናል። በቅድስ ቁራን እንደተጠቀሰው (49፡9) ሁለት የእምነት ወገኖች ቢጣሉ በመሃል ግቡና አስማሙ፤ ከመካከላቸው አንዱ በሌላው ላይ እንደገና መጥፎ ቢሆን የአላህን ሕግ እስከሚያከብር ድረስ ተዋጉት። ከተመለሱ በመካከላቸው በፍትህ አቀራርቧቸው። ለፍትህ ሚዛን ስጡ፤አላህ ለፍትህ ሚዛን የሚሰጡትን ይወዳቸዋል” የአላህ/የእግዚአብሔር ትእዛዝ የሚለው ለሰው ፍጡር ዋጋ ስጡ ነው ለዚህም ነው “ፍትህን ሚዛን ለሚሰጡ ወዳጇቸው” ያለው ኢትዮጵያውያን ምንም አይነት የእምነት ይኑረን ውይም በእምነት እንለያይ እርስ በእርሳችን ልንረዳዳ ይገባል። አንዱ በሌላችን ላይ አፍራሽ ነገር ቢኖርው ይህን አስተሳሰብ እንዲያርም መርዳት ይኖርብናል። እስላምን ለመደገፍ እስላም መሆን የለብህም ክርስቲያንን ለማገዝ ክርስቲያን መሆን የለብህም ወይንም አኘዋክን ለመርዳት አኘዋክ መሆን የለብህም እንዲሁም አማራ አማራን ኦሮሞ ኦሮሞን መሆን የለበትም። ይህም የኛን ቤተሰብን፤ ጎረቤትን ወይንም ያቅራቢያችን ብቻ ሳይሆን ሁላችንም በፍቅር ልንስተገድበት የምንችልበት ሰፋ ያለ ቤት መሆብን አለበት ኢትዮጵያ የሁሉም ሀገር ናት። ሁሉም ዘርና መሰረት ሳይለይ መተባበር ይኖርበታል።

መለስና ኢህአዴግ እውነተኛ ኢትዮጵያውነታችን ሰርቀው በመካከላችን ሊከፋፈሉን በመጣር ላይ ናቸው። እንዴት ነው የአንድ ሀገር ቤተሰቦችን ከመበተን የምንጠብቀውና መጭውን ትውልድ በአንድነት እንደተሳሰረ እንዲኖር ማድረግ የምንችለው? የመለስን ጥፋት ልናስቆመው የምንችለው፤ ጎረቤታች እንደራሳችን አድርገን ስንወድ ነው። ይህንንም ለማድረግ ጥላቻን፤ በኩንነትን፤ ፍትህ መጉደልን፤ የዘር ጭፍጨፋን፤ ስግብግብነትን ውሸትን ወይም ምንም ሳይሰሩ መቀመጥን በመዋጋት ልንከላከለው እንችላለን። በቁራን (2፡263) “መልካም ንግግርና ይቅርታ ማድረግ አቁስሎ እርዳታ ከመስጠት የተሻሉ ናቸው። አላህ በራሱ ባህሪ ብቁ ነው ይህንን ለመሸከም’ ይላል

በእንግሊዝ የፀረ-ባርነትና የአሜሪካው የሰባአዊ መብት ንቅናቄዎች ሁሉም መሰረት ያደረጉት የመፅሃፍ ቅዱስ መርህን መሰረት ያደረጉ ከአባያተ ክርስቲያናትን የፈነዱ ናቸው። ማልኮሊን ኤክስ የፍትህና የእኩልነት መልክት ከእስላሙ ማህበረሰብ ተነሳ በዚህም አፍሪካ አሜሪካን ለእኩልነት፤ ለሰብአዊ መብት መከበርና ለፍትህ አነሳሳ። ሬቨረንድ ማርቲን ሉተር ኪንግ የለምንም ፍራቻ አድልወን፤ ሰዎችን ማጣጣልንና የንቀት አመለካከቶችን በክርስቶስ ወንጌል ሰበካው በሰላማዊ ሁኔታ ተቃወመ።

ማህተመ ጋንዲ በፀረ አመፅ የሕንድ ትግላቸው ይዘውት የተነሱት የተለያዩ የሀይማኖት መረጃዎችን ነው። ሕዝባቸውንም ለቂም በቀል እንዳይነሳሳ አስተማሩ እንዲህም አሉ “አይንን በአይን ጥርስን በጥርስ በማጥፋት መልስ መስጠት አለምን መብያ ማስቀረት ነው” ሰብአዊነት እና ከጥላቻ በመራቅን ተመርኩዘው ኒልሰን ማንዴላ የሰጡት አመራር ሕዝባቸውን ሳይከፋፈል እንዲኖር አስችሏል። በአሁኑ ወቅትም ቅዱስ ዳሊላማ በቲቤት ያለ አመፀ ለነፃነት ለእኩልነት እና ለፍትህ የሕዝባቸውን ትግል በመምራት ላይ ናቸው።

እነዚህ ምሳሎዎች ሁሉ የሚነግሩን ጉዳይ አለህ/ እግዚአብሄር የሰውን ሕልውና ሲፈጥር በነፃነት ነው በእንደዚህ አይነት ወቅት ይህ ነፃነት ከፍተኛ መስዋእትነት ሊጠይቅ ይችላል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንን አይነት ቆራጥ አመራር ከሀይማኖት መሪዎች ይፈልጋል። በእነዚህ አካባቢ እየታየ ያለው የስህተት መንገድ እንዲታረም አሁንም ቁራን እንዲህ ይላል 4፡27 አላህ “ወደ አንተ የምረት ፊቱን ያዞራል ይህን ለመከተል ፍላጎት ላላቸው ሁሉ ታላቅ ሰላም የተረጋጋ ሁኔታ መፈጠር አለበት።”

በሕዝቦች ልቦና ውስጥ አላህን በሚከተሉና በአለም ላይ ግፊት በሚያደረጉ መካከል ጦርነት ይካሄዳል። በእኛ ሁኔታ የጭቆና አገዛዝ አካል አንሆንም ብለን ልንቃወም ይገባል። ከመካከላቸሁ ያሉ መምህራን ይህንን ምዕራፍ አባባል ትርጉመው ቢያስተምሩአችሁ ጥሩ መልክት ያለው ነው።

በመላ አለም በመጥፎ ምግባር የተሰማራውንና ሌሎችን ለመርዳት ደንታ ቢሱን ወገን ስለትክክለኛ አሰራር እና በመፈቃቀር አብሮ መኖርን ከእኛ መስጊድና ቤተክርስቲያን ቀሪው አለም እንዲማር ኢትዮጵያውያን ይፈልጋሉ። ብዙዎቹ የጊዜው ሰዎች በእኛ ሕብረተሰብ መካከል ድህውን፤ ደካማውንና የተጨቆነውን ድጋፍ ይነፍጉታል። ይህ ግን የእውነተኛ እምነት ተከታዮች ምግባር አይደለም። ሁላችንም የአላህ ብርቅዬ ልጆቹ ነን እርሱም ሁሉንም ያውቃል በተለይ የእርሱን እርዳታ ሽተው ለሚያለቅሱ በሚገባ ያዳምጣቸዋል/ይሰማቸዋል። እኛም እነዚህን የሚያነቡትን ሰዎች እናዳምጣቸው አላህ ወይም እግዜብሄር ፍቅሩን ለእነርሱ ይለግሳልና።

በቅዱስ ቁራን (3፡92) “በምንም ሁኔታ ትክክለኛን ፈለግ ተከተል የምታፈቅረው ጋር አብረህ እስከምትውል ድረስ ምንም ነገር ብትሰጥ አላህ በእርግጠኝነት ያውቀዋል።” በዚህ አስቸጋር ዘመን ኢትዮጵያውያን እስላሞች ለሀገራችን ብዙ አስተዋኦ ይጠበቅባቸዋል/ ይኖራችኃል። አስቡ እስኪ በዚህ ጉባኤ የተሳተፉት ሁሉ የኢትዮጵያ ሞስሊሞች ለሰበአዊ መብት መከበር ለፍትህ ለዴሞክራሲና ለነፃነት እንዲቆሙ የሚያስችል አንድ ንቅናቄ ብትመሰረቱ የሚያመጣውን ለውጥ አስቡ፤

አሁንም ገምቱ እስኪ የኢትዮጵያ እስልምና ጉባኤ ተሳታፊዎች ሌሎች የእምነት ተከታይ ወገኖችን የሚያጠቃልል ጉባኤ ብትጥሩ ማለትም ከእስልምና ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ፣ ከይሁድ፣ ከኢቫንጂሊካን ከባህላዊ እምነት ተከታዮች እና ሌሎችንም ለአዲስቱ ኢትዮጵያ ግንባታ አብራችሁ ብትሰሩ የሚያመጣውን ለወጥ አጢኑት የአዲሱቷ ኢትዮጵያ የትብብር ንቅናቄ አባላት እንድትሆኑ ጥሪያችንን እናቀርባለን። የእምነት ማህበረሰብ ለኢትዮጵያና ለአፍሪካ ቀንድ እርቅ እና ሰላም ለማምጣት በጣም ጠቃሚ ነው።

የሀገራችን ሕዝብ የወደፊት መፃኤ እድል ለመወሰን በእምነቱ ዙሪያ እንዲሰባሰብ ለማድረግ መሽማቀቅ የለብንም። የእምነቱ መግለጫ ቦታወች በነጻነት መንቀሳቀሻ መሆን አለባቸው።የእምነት ተቋማት መንግስት እንሁን አይደለም ጥያቄው። ሕዝቡ ግን በአግባቡ የመንግስትን አሰራር ስርአዓት ማስያዝና ለሚሰራውም ተጠያቂ እንዲሆን የሚጠይቁና መፈጸሙንም የሚከታተሉ መሆን አለባቸው።

በሌላ በኩል ድግሞ መንግስት የሀይማኖት ተቋማትን ማዋከብ፣ የሚሰሩትን ተግባር በነፃ ስሜት እንዳያካሂዱ መቆጣጠር የለበትም። ሕዝብ በአግባብ እንዲመራ በመስጊድ ወይም በቤተክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ከቅጥር ግቢ ውጭም ጭምር ይኸ ተግባራዊ መሆን አለበት። መለስና የእርሱ መንግስት በአንዳድ አካባቢዎች የእስልምና እና የክርስትና መሪዎች በፍራት፣ በመደለያ፣ በወከባና በስጋት ከእነርሱ ጋር ሆነው እንዲሰሩ መቆጣጠር ተሳክቶላቸዋል ምክንያቱም ሃይማኖት ፍትህ ሲዛባ ተቃዋሚ እንደሆነ ያወቃሉ። በከፍተኛ የሚሰጉት የአካል ጠንካራውንና የሚሳደበውን አይደለም የሞራል ብርቱዎችናን እውነተኛዎችን ነው። ይህን በማድረግም መሪዎችንና አማኞችን የቁራንንና የመፀሀፍ ቅዱስን መርህ እንዳይከተሉ ግፊት እና ጫና ያደረጉባቸዋል።

እምነት ፍትህ በሚያጓድል ስርዓት ጫና ሊደረግበት አይገባም። አንዳንድ ጊዜ በማዋከብ ፀጥ ለማድረግ ይህም ሀቀኛ ባህሪውን እንዲያጣና በማህበረሰብ ሕይወት ውስጥ ዋጋ ያለሽ እንዲሆን ያደርጋል። መፀሀፍ ቅዱስም ሆነ ቁራን በነፃ ለአላህ/ ለእግዚአብሂር የማይቀርብን እምነት ያወግዙታል ምክንያቱም በሀቅ መኖር ያቃተው ዋጋ ቢስ በመሆኑ ነው። በቁራን እንደተገለጠው 2፡256 “በእምነት(በሀይማኖት) ግዴታ የለም” ይላል

በክርስቶስ ትምህርት አማኞች “ጣፋጭነታቸውን” ማጣት የለባቸውም በማህበረሰብ ውስጥ ምንም መስዋዕትነት ቢጠይቅ መጥፎና ደጉን እንደሁኔታው ማሳየት ይኖረባቸዋል። ብዙ ሰዎች በመፀሀፍ ቅድስና በቅዱስ ቁራን መርሆዎች ለችግሮቻቸው መፍትሄ ይሰጣሉ በሕዝብም መካከል መከበርና ፍቅር ያተርፋሉ።

ኢትዮጵያ ሁል ጊዜም የተለያዩ ባህሎችና እምንቶች ያጌጠች ሀገር ናት። ኢትዮጵያ የእነዚህ ሁሉ ቤት በመሆኗ እና የእነርሱ ልጆችም በደስታ የሚኖሩባት እንድትሆን እና እንዴት አብሮ መኖር እንደለብን መማር ያለብን ግዴት ነው። የኢትዮጵያ እሳልምና ሀይማኖት መራዎችም ይህን ማገዝ ይኖርባቸዋል።

ተስፋ እንደማደርገው ለዘመናት በፍቅር አብሮ መኖርን ውርስ የእናንተ ተከታዮች ግንባር ቀደም ሆነው እንዲቁጥሉና ሌሎች እምነት ተከታዩችን ተመሳሳይ በፍቅር አብሮ መኖርን እንዲያድሱ ታደፋፍራላችሁ ብዩ ተስፋ አደርጋለሁ። እኛ አሁን አንድነቱ የላላውን ሕብረተሰብ እና የቆሰለውን ልባችን ለመጠገን የእናንተን እርዳታ እንፈልጋለን። እንደ ሕዝብና እንደ ሀገር መኖር ካለብን አሁን ወሳኝ ጊዜ ላይ ነው ያለነው። በአሁኑ ወቅት የምንቋቋማቸው ችግሮች እና መልካም ገጠመኖች አሉ። ለሌሎችም ልንተዋቸው አንችልም ወይንም ማስጠንቀቂያውን እየሰማን ቸል ብለን ልናልፍ አንችልም ምክንያቱም መጭው ጊዜ ከአላህ/ ከእግዜብሂር ጎን የቆሙ ሰዎች እርዳታ ካልታከለበት በጣም ረዥምና አድካሚ ፈተና ተደቅኖብናል፣ ልንወጣውም አንችልም። በሰላም ማስፈኑ የኢትዮጵያ እስላሞች በመሪነቱ ቢካፈሉ በቀሪው አለም ላለው ወገንም ወርቃማ ታሪክ ያስተምራሉ። የደንቆሮዎችን አስቀድሞ በሞስሊሙ ህብረተሰብ የመፍረድ ፍርደ-ገምድል ባህሪም ያሽማቅቃል። ሕብረተስቡም በነፃነትና በሰላም ይኖራል።

አላህ/ እግዚአብሔር የእርሱ እምነት ሀቀኛ ተከታዮች እንድንሆን ይሻል። ይህን ሁሉ ስናደርግ ሰላምን፤ ፍትህን፤ ነፃነትን፤ ሞራልን ከሁሉ በላይ ደግሞ የእግዚአብሄርን መፍራትና የአላህ ፍቅር ለውድ ሀገራችን ኢትዮጵያ እንዲሰጥ እንመኛለን ።

አላህ/ እግዜብሄር የእርሱ መልካም ምህረትና ፍቅር ታክሎበት የአሁኑንና የነገውን ችግራችን ለመቋቋም ብሎም ተስፋችን እንዲለመልም ጥንካሬን ጥበብንና ቅዱስነትን ለኢትዮጵያ ሞስሊሞች ስጣቸው። በአላህ ስም ምህረትና ትህትናን እንለምን።

ለሌሎች መረጃዎች አቶ ኦባንግ ሞቶን በዚህ አሜል አድራሻ ይጠይቁ። obang@anuakjustice.org